## ከኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የአዲስ አበባ ጽ/ቤት ሚያዚያ 5 ቀን 2000ዓ.ም. የተካሄደውን ምርጫ አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

በአዲስ አበባ ከተማ ሚያዚያ 5 ቀን 2000ዓ.ም. ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማሟያና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የተካሄደው ምርጫ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል:: በዚህ ምርጫ በምዝገባው ወቅት ለመራጭነት ከተመዘገቡት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ከሚሆኑት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች መካከል 87 በመቶው ይወክሉናል ላሏቸው እጩዎች ድምጻቸውን ሰጥተዋል:: ምርጫው ያለምንም ሳንካ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ አግባብ ተፈፅሟል::

በዚህ ምርጫ ከ1997 ምርጫ ማግስት በታየው ትርምስ ምክንያት ብዙዎች የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ዳግም ለምርጫ አይወጡም በማለት ያራምዱት የነበረው ግምት ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል:: ከዚህም አልፎ በ97 ምርጫ የታዩ ችግሮችን መነሻ በማድረግ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ወደኋላ ተመልሷል የሚለው የአንዳንዶች ግምት ስህተተኝነት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የዘንድሮው ምርጫ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ስር እየሰደደና እየተጠናከረ እንደሚገኝ አመላክቷል:: ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለመራጭነት መመዝገባቸውና ከዚህም ቁጥር መካከል እጅግ በርካቶች ድምፃቸውን መስጠታቸው የሚያመላክተው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ዴሞክራሲ የፍላጐታቸው ማስፈፀሚያና ለልማትና ለመልካም አስተዳደር ለሚያካሂዱት ትግል መሳሪያ መሆኑን መገንዘባቸውን ነው::

**የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች!**

ኢህአዴግ መላው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የዘንድሮው ምርጫ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ አግባብ እንዲፈፀም ባደረጋችሁት ተሳትፎ ምርጫው በመሳካቱና በከፍተኛ ቁጥርም ወጥታችሁ በመብታችሁ በመጠቀማችሁ ያለውን ልባዊ አድናቆት ይገልፅላችኋል:: በዚሁ ምርጫ ለከተማችን ነዋሪዎች ዘላቂ ፍላጐቶች መጠበቅና ለጥቅሞቻችሁ መረጋገጥ የነደፈው ፕሮግራም በከተማዋ ይፈፀም ዘንድ ከተማዋን እንደገና እንዲያስተዳድር እድሉን ስለሰጣችሁት ኢህአዴግ የአክብሮት ምስጋናውን ሊያቀርብላችሁ ይወዳል::

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በምርጫው በስፋት በመሳተፍ እጩዎቻችንን በከፍተኛ ድምፅ ለምን እንደመረጡም ኢህአዴግ ጠንቅቆ ይገነዘባል:: ኢህአዴግ አዲስ አበባን ባስተዳደረባቸው አመታት በተለይም በመጨረሻዎቹ ሁለት ተኩል አመታት ጀምሯቸው በነበሩት የልማት ፕሮግራሞች ከተማችን የለውጥ ብርሃን አይታ እንደነበር ይታወቃል:: የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ኢህአዴግን የመረጡት ይህ ለውጥ እንዲቀጥል ከፍተኛ ፍላጐት ስላላቸው ነው:: ኢህአዴግ ጀምሮት በነበረው ልማት ቁጥሩ የማይናቅ የህብረተሰብ ክፍል

ተጠቃሚነቱ እንደተረጋገጠ ቢታወቅም አሁንም በሚፈለገው መጠን ፍላጐታቸው ያልተሟላ በርካታ ነዋሪዎች እንዳሉና ልማቱም ቀጣይ ሆኖ ሁሉም የከተማችን ነዋሪዎች የልማቱ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው በነዋሪዎች ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ልባዊ ፍላጐት ኢህአዴግ ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም ኢህአዴግ ጀምሯቸው የነበሩት የልማት ጥረቶች ተጠናክረው ፈጣንና ሰፊ በሆነ አግባብ መከናወን እንዳለባቸውና የነዋሪዎችም ተጠቃሚነት መረጋገጥ እንደሚኖርበት ለዚህም መሳካት ድርጅታችንና ነዋሪዎች ተቀራርበው በጋራ መስራት እንዳለባቸው ኢህአዴግ በፅናት ያምናል፡፡

ከመልካም አስተዳደር አኳያም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ባስተዳደረባቸው አመታት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበትን አሰራር ለማስፈን፣ ሙስናን ለመቆጣጠር፣ ህገወጥነትን ለመግታትና ህዝብንም ለማሳተፍ መጠነ ሰፊ ጥረት አድርጐ የነበረ ቢሆንም በ97ቱ ምርጫ ከተማዋን ለማስተዳደር እድል በማጣቱ ከዳር ሊያደርሰው ያልቻለውን ጥረቱን አጠናክሮ ሊቀጥልበት እንደሚገባ የነዋሪዎች ፍላጐት መሆኑን ኢህአዴግ ይገነዘባል፡፡ የከተማችን ነዋሪዎች የመልካም አስተዳደር ፍላጐቶች እንዲሟሉም በሌሎች የሀገራችን ከተሞችና ገጠሮች ተስፋ ሰጪ በሆነ አግባብ በመፈፀም ላይ ያለው የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራም በከተማችንም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፣ ይህ እንዲሳካም ኢህአዴግ ነዋሪዎችን ይዞ መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅበት በፅናት ያምናል፡፡

**የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች!**

በአዲስ አበባ ከተማ የሚታዩት የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እጅግ የተወሳሰቡና ሰፊም መሆናቸውን ኢህአዴግ ጠንቅቆ ይገነዘባል፡፡ እነዚህ ችግሮች በአንድ ወገን ጥረትና በአንድ ጀምበር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችም አይደሉም፡፡ የከተማችን ነዋሪዎች የልማት ተጠቃሚነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ በተግባር ተፈትነው ውጤታማነታቸው የተረጋገጠውን የኢህአዴግን ፖሊሲዎች ተግባራዊ ለማድረግ ብቁ አመራርና የተደራጀና የተባበረ የነዋሪዎች ጥረት እጅግ ተፈላጊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ኢህአዴግ በአስተዳደሩ ላይ በተቻለ መጠን ለውጥ በማምጣትና በዚህ ምርጫ ያገኘውን እድል በመጠቀም የመረጣችኋቸውን ተወካዮቻችሁን አቅም ብቻ ሳይሆን መላ ድርጅታዊ አቅሙን አስተባብሮ የልማትና የመልካም አስተዳደር ፍላጐቶቻችሁን ለማሟላት ጠንክሮ ለመስራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ ሆኗል፡፡ ይህም ሆኖ የኢህአዴግ ጥረት ብቻውን ረዥም ርቀት ሊወስደን እንደማይችልና ከእናንተ የተደራጀ ተሳትፎ ውጪ ችግሮች ሊፈቱ እንደማይችሉ ተገንዝባችሁ በተደራጀ አግባብ ከጐናችን በመቆም የመፍትሔ አካል ትሆኑ ዘንድ ኢህአዴግ ዛሬም በድጋሚ ጥሪውን ያቀርብላችኋል፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ ካለፈው አመት ጀምሮ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ታምኖበት የተደራጁት የወጣቶች፣ የሴቶችና የነዋሪዎች ፎረሞች ተልእኮዎቻቸውን ለመወጣት አበረታች እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ይገኛሉ። ኢህአዴግ እነዚህ የምክክር መድረኮች በቅርቡ በሚቋቋመው የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤትም እውቅና አግኝተውና ይበልጥ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብሎ ያምናል። ፎረሞቹም ሆነ ሌሎች ህዝባዊ አደረጃጀቶች በከተማችን ለሚካሄደው የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ ብቁ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችሉም ዘንድ መጠናከር ይኖርባቸዋል። ኢህአዴግ በሚመራውና በቅርቡ በሚቋቋመው አስተዳደር አማካኝነትም ፎረሞችንና ሌሎች ህዝባዊ አደረጃጀቶችን ለማጠናከርና የልማትና የመልካም አስተዳደር ብቁ አቅሞች እንዲሆኑ ለማድረግ ተግቶ ይሰራል። በአጠቃላይም በምርጫ ካርዳችሁ የሰጣችሁትን አደራ ከሁሉም የከተማችን ነዋሪዎች ጋር በመሆን በብቃት ለመወጣት ተዘጋጅቷል።

**የተከበራችሁ የከተማችን ነዋሪዎች!**

ኢህአዴግ ከተማችንን በእድገትና ህዝብ ተጠቃሚ በሚሆንበት ጐዳና እንዲመራ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የከተሞችን እድገት ለማፋጠን ባደረገው ርብርብ ያካበተውን የመምራት ችሎታና ልምድ ለእድገታችሁና ለላቀ ተጠቃሚነታችሁ እንዲያውለው የሰጣችሁት ይሁንታ ውጤታማ ይሆን ዘንድ በሚያደርገው ጥረት ከጐኑ እንደማትለዩ ያለውን ልባዊ እምነት ይገልፅላችኋል። ከእናንተው ጐን ሆነን የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚዎች እንድትሆኑ ለማድረግና ከተማችንም ሀገራዊ፣ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ተልዕኮዎችዋን የመወጣት ብቃት በምትጐናፀፍበት ጐዳና ለመምራት ያለውን ቁርጠኝነትና ዝግጁነት በድጋሚ ያረጋግጥላችኋል። በዚህ አጋጣሚ የኢህአዴግ የአዲስ አበባ ጽ/ቤት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልፃል።

ሚያዚያ 16 ቀን 2000 ሊ.ም.
አዲስ አበባ